የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የቀድሞ የፌዴራል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ
# የ2011 በጀት ዓመት የ8 ወራት ሂሳብ
# ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት /2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የቀድሞ የፌዴራል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ

# የ2011 በጀት ዓመት የ8 ወራት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የፌዴራል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ የተመደበለት መደበኛ በጀት በፋይናንስ አዋጅ፤ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የ8 ወራት የሂሳብ ሪፖርቶች እና ማስታወሻዎች ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለማቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጠጋቢ የሆነ ማረጋገጫ ( የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የቀድሞ የፌዴራል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት የኤጀንሲው የ2011 በጀት ዓመት የ8 ወራት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የኤጀንሲው የ8 ወራት የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ደንብ መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**የወጪ ሂሳብ**

1. ከኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ደመወዝ ብር 2,994.24 የህክምና መዋጮ ተቀናሽ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡
2. ኤጀንሲው ግልጽ ጨረታ ሳያወጣ በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 510,649.80 ተገኝቷል፡፡
3. ኦሪጅናል ማስረጃ ሳይቀርብለት የውሎ አበልና የትራንስፖርት ወጪ ሂሳብ በድምሩ ብር 630,863.66 በፎቶ ኮፒ ማስረጃ ተወራርዶ ተገኝቷል፡፡
4. የአጥር ሽቦ ግዥ በብር 24,500.00 የተፈፀመ ቢሆንም ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ የካቲት 30/2011 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤**

5. በድምሩ ብር 482,424.96 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች ተገኝተዋል፡፡
6. በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ በ9 ወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 94,348.62 ክፍያዎች ተፈጽመው ተገኝቷል ፡፡

**ሌሎች ጉዳዮች**

**የንብረት አስተዳደርና አጠባበቅ በተመለከተ**

7. የቋሚ እቃ እና አላቂ በአንድ ላይ ተከማችቶ መገኘቱ፡፡
8. በየዓመቱ የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ የማይካሄድና ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፡፡
9. አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች አገልግሎት ከሚሰጡ ንብረቶች ተለይተው ያልቀመጡ መሆኑ ፤
10. በቋሚ ንብረት መጋዘን የተለያዩ ወንበሮች ፤ላፕቶፕ ስልክ ሃርድ ዲስክ የሚወገድና ተጠግኖ አገልግሎት የሚሰጡ መገኘቱ ታውቋል፡፡

**አንድነት ብዙሰው**

ከሠላምታ ጋር

**ቀን ---------**